# [በሴት ብልት ግርዛት ወይም መቁረጥ (FGM/C) ላይ ያለው መረጃ]

## የሴት ብልት ግርዛት ወይም መቁረጥ (FGM/C) ምንድን ነው?

የዘመነው የ2022 *[U.S. በስርዓተ-ፆታ ላይ የተመሰረቱ ጥቃቶችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመከላከል እና ምላሽ መስጠት ስትራቴጂ]* መሰረት የውጪ ጉዳይ መስሪያ ቤት የሴት ብልት ግርዛትን እና መቁረጥን (FGM/C) ውጫዊ የሴት ብልትን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ወይም የሕክምና ባልሆኑ ምክንያቶች በሴት ብልት አካላት ላይ የሚደርስ ጉዳት ሲል ይገልጸዋል። FGM/C በአይነተኛነት የሚፈጸመው ከህጻንነት እስከ አዋቂ ሴቶች በወጣት ልጃገረዶች እና አልፎ አልፎ በአዋቂ ሴቶች ላይ ነው። FGM/C የሰብአዊ መብት ጥሰት እና ጾታን መሰረት ያደረገ ጥቃት ነው። ልልምዱ ምንም አይነት የጤና ጥቅሞች የለውም ስለሆነም ወዲያውኑ የሚከሰት እና ረጅም ጊዜ የሚቆይ የአካል እና የአዕምሮ ጤና ችግሮች ሊያስከትል ይችላል። FGM/C ዛሬ በህይወት ባሉ ከ200 ሚሊዮን በላይ በሚሆኑ ሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ተጽእኖ እንደፈጠረ ይገመታል። የሴት ብልት ግርዛት ወይም መቁረጥ (FGM/C) ምክንያቶች ከቦታ ቦታ የተለያዩ እና በቤተሰብ እና በማህበረሰቦች ውስጥ የተለያዩ የማህበራዊና ባህላዊ የአስተሳሰብ ውሁዶችን ያካትታሉ።

## FGM/C በጤና ላይ የሚያደርሱት ጉዳቶች ምንድን ናቸው?

ወዲያውኑ የሚደርሱ ጉዳቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤ እነሱም የደም መፍሰስ፣ ከባድ ህመም፤ ትኩሳት፤ ድንጋጤ እና አንዳንድ ጊዜም ሞት ናቸው። የረጅም ጊዜ የጤና ችግሮች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፤ እነሱም የሽንት ወይም ሌሎች ኢንፌክሽኖች፣ መሃንነት፣ የሚያሰቃይ የወር አበባ ወይም የግብረ ሥጋ ግንኙነት እና ከግዜ በኋላ የቀዶ ጥገና አስፈላጊነት ናቸው። በተጨማሪ FGM/C የተደረገባቸው ሴቶች እና ልጃገረዶች በወሊድ ጊዜ ለሚፈጠሩ ችግሮች የበለጠ የመጋለጥ እድል ያጋጥማቸዋል እንዲሁም ህጻናት ልጆቻቸው በልምምዱ ምክንያት የመሞት እድላቸው ከፍ ያለ ነው። በመጨረሻም ልምምዱ ልጃገረዶች እና ሴቶች ላይ የረጅም ጊዜ የስነ-ልቦና ተግዳሮቶችን ማለትም ድብርት፣ ጭንቀት፣ ድኅረ-አሰቃቂ ጭንቀት፣ በራስ የመተማመን ማጣት ስሜት ወይም ሌሎች ፈተናዎችን ጨምሮ ሊጭንባቸው ይችላል።

## FGM/C ላይ የU.S. መንግስት ያለው አመለካከት ምንድን ነው?

FGM/C ምንም ዓይነት ይሁን፤ ደረጃው ወይም የአስከፊነቱ ወይም ለማድረግ የሚያነሳሱ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ ወይም ሌሎች ምክንያቶች ቢኖሩም የU.S. መንግስት FGM/Cን ይቃወማል። የU.S. መንግስት FGM/C የሰብአዊ መብት ጥሰት እና ጾታን መሰረት ያደረገ የሁከት ዓይነት እንደሆነ እና የህጻናት ጥቃት አድርጎ ይመለከተዋል።

## የU.S. መንግስት ይህንን የFGM/C ማሳሰቢያ የሰጠበት ምክንያት ምንድን ነው?

የU.S. መንግስት FGM/Cን ለማስቆም ቁርጠኛ አቋም የወሰደበት ምክንያት በአለም አቀፍ ደረጃ የልጃገረዶች እና የሴቶች ጤንነት እና ደህንነት ለማስጠበቅ እና መብቶቻቸውን ለማረጋገጥ ነው። ዩናይትድ ስቴትስ FGM/C በልጃገረዶች እና ሴቶች ላይ የሚያስከትለውን ከባድ እና ጎጂ የሆኑ ውጤቶችን በተመለከተ ህዝብን ለማስተማር በአገር ውስጥም ሆነ በሌሎች ሀገራት ላይ FGM/Cን ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት እየሰራ ይገኛል።

## FGM/Cን መፈጸም ወይም ድርጊቱ እንዲፈጸም ተባባሪ መሆን የሚያስከትላቸው ሕጋዊ መዘዞች ምንድን ናቸው?

ከ18 ዓመት በታች የሆነች ልጃገረድ ላይ FGM/Cን መፈጸም፣ ለመፈጸም መሞከር ወይም ለመፈጸም ማሴር ወይም ለFGM/C ሲባል ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ መላክ (18 USC § 116) በU.S. ህግ የተከለከለ ነው። እንዲሁም በወላጅ፣ በአሳዳጊ ወይም በተንከባካቢ FGM/C እንዲፈጸም ማመቻቸት ወይም መስማማት በህግ የተከለከለ ነው። ሕጉን መጣስ እስከ 10 አመት የሚደርስ እስራት፣ የገንዘብ መቀጮ ወይም ሁለቱንም ያጣመረ ቅጣት ያስከትላል። በሃይማኖት፣ በልማድ፣ በሥርዓት፣ በወግ ወይም በመደበኛ ልምምድ ምክንያት FGM/C መፈጸምን ሕጉ የተለየ አስተያየት አያደርግለትም። በተጨማሪም 41 ስቴቶች FGM/C በወንጀል የሚያስጠይቅ ሕጎች አሏቸው እና FGM/C በሁሉም ስቴቶች የተከለከለ የሕፃናት ጥቃት ዓይነት ነው።

## የFGM/Cን የሚከለካሉ ሕግጋት መጣስ በኢሚግሬሽን ሁኔታዎ ላይ የሚያስከትሏቸው መዘዞች ምንድን ናቸው?

FGM/Cን የሚከላከሉ ሕግጋትን መጣስ – በፍርድ ቤት በወንጀል ጥፋተኛ ሆነው ባይገኙ እንኳን – ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንዳይገቡ ማገድ ወይም ከዩናይትድ ስቴትስ እንዲባረሩ እና አንዳንድ የኢምግሬሽን ጥቅማ ጥቅሞች ከማግኘት ብቁ አለመሆንን ጨምሮ፤ የኢምግሬሽን ሁኔታዎን የሚነኩ አሉታዊ መዘዞችን ሊያስከትሉ ይችላሉ።

## FGM/C የተፈጸመባቸው ሴቶች እና ልጃገረዶች ሕግን ጥሰዋል?

FGM/C የተፈጸመባት ግለሰብ ጥፋተኛ አይደለችም። ሂደቱ እንዲፈጸምባቸው በመደረጉ ምክንያት የሚጥሷቸው ምንም የU.S. ሕጎች የሉም። FGM/C የተፈጸመባቸው ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የመጓዝ ወይም የኢምግሬሽን ጥቅማ ጥቅሞች የማግኘት ብቁነታቸው ላይ አሉታዊ ውጤት አይኖረውም። FGM/C የተፈጸመባት አንዲት ግለሰብ ለተወሰኑ የኢሚግሬሽን ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ እና ስለ ኢሚግሬሽን የእርዳታ አማራጮች ጥያቄ ካላቸው ብቃት ካለው ጠበቃ ወይም እውቅና ካለው ተወካይ ጋር መማከር አለባቸው።

## አንድ ግለሰብ ተጨማሪ ግብአቶን ከየት ማግኘት ይቻላል?

ምናልባት FGM/C ሊፈጸምብኝ ይችላል ብለው የሚያምኑ ከሆነ ወይም FGM/C ከተፈጸመብዎት፣ ወይም FGM/Cን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ካልዎት፣ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ FGM/C የሚፈጽም ሰው የሚያውቁ ከሆነ፣ ወይም በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ወይም ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ ለዚህ አደጋ የተጋለጠች ሴት የሚያውቁ ከሆነ፣ እባክዎን 800-225-5324 (FBI)፣ 866-347-2423 (DHS ICE Homeland Security Investigations)፣ 800-4-A-Child (800-422-4453) ወይም U.S. End FGM/C Network (endfgmnetwork.org) በመጠቀም ግንኙነት ይፍጠሩ። ምናልባት በውጭ አገር FGM/C ይፈጸምብኛል ብለው ስጋት ውስጥ ያሉ የUS ዜጋ ከሆኑ ወይም የሚያውቁት የUS ዜጋ ካለ፣ እባክዎን በአቅራቢያዎ የሚገኘውን የU.S. ኤምባሲ ወይም ቆንስላ ወይም የU.S. የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የውጭ አገር ዜጎች አገልግሎት ቢሮን በ(888) 407-4747 (ከU.S. ወይም ካናዳ) ያግኙ። ወይም (202) 501-4444 (ከውጭ አገር)። ለበለጠ መረጃ እባክዎን https://www.uscis.gov/FGMC ይጎብኙ።